# ጋዜጣዊ መግለጫ

**(አዲስ አበባ ህዳር 04/2018 ዓ.ም)፥**

## አዋሽ ባንክ እና የጤና ሚኒስቴር በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የሥራ ውል ስምምነት ተፈራረሙ

የኢፌዲሪ የጤና ሚኒስቴር እና አዋሽ ባንክ የዲጂታል ጤና ክፍያን በአዋሽ ባንክ የዲጂታል ባንክ አማራጮች ለማስጀመር የሚያስችል የሥራ ውል ስምምነት በዛሬው እለት በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ተፈራርመዋል፡፡

የፊርማ ሥነ-ስርዓቱ በጤና ሚኒሴቴር ሚኒስትር ክብርት ዶ/ር መቅደስ ዳባ እና በአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ ክቡር አቶ ፀሐይ ሽፈራዉ መካከል ተካሂዷል፡፡

በስምምነቱም የጤና ነክ ክፍያዎች ባንኩ ያሉትን ዘመኑን የዋጁ የዲጂታል አማራጮችን በማቅረብ በጤና ተቋማት ማለትም በሆስፒታሎች እና በጤና ጣቢያዎች ላይ የሚደረጉ ክፍያዎችን በማዘመን ቀላል እና ለሁሉም ምቹ በሆኑ የዲጂታል አማራጮች ክፍያዎችን እንዲከፍሉ የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል።

አጠቃቀሙም የባንኩ ደንበኞች የጤና ክፍያዎቻቸውን በአዋሽ ብር-ፕሮ (Awashbirr-pro) የሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያ በመጠቀም በኪው-አር ኮድ (QR code) እንዲሁም በጤና ባለሙያው የደንበኛውን ስልክ በመጠቀም በ (USSD) ወደ ደንበኛው የክፍያ ጥያቄ በመላክ፣ ደንበኛው የራሱን የይለፍ ቃል እንዲያስገባ በማድረግ ብቻ ክፍያ መፈጸም የሚያስችል ነው።

በመግባቢያ ስምምነቱ ላይ ክብርት ሚኒስትሯ ዶ/ር መቅደስ ዳባ በንግግራቸው እንደገለጹት የጤና ዘርፍን ለማሻሻልና አገልግሎቶችን ዲጂታል ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው እንደ አዋሽ ባንክ ያሉ ግዙፍ የፋይናንስ ተቋማት የዲጂታል ክፍያ ሥርዓት በእጅጉ እንዲስፋፋና እንዲጎለብት እየተጫወቱት ያለዉ ሚና እጅግ አበረታች እና ዕዉቅና የሚሰጠዉ መሆኑን ተናገረዋል፡፡

የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራዉ በበሉላቸው አዋሽ ባንክ ለደንበኞቹ የሚሰጠውን የባንክ አገልግሎት በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፈ እና ዘመኑን የዋጁ አዳዲስ፣ ምቹ እና ቀልጣፋ አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ስራ አስፈፃሚው አክለውም የዲጂታል አገልግሎቶቹን ተደራሽ፣ ምቹ እና ቀልጣፋ ለማድረግ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የጤና ነክ ክፍያዎችን በአዋሽ ብር ፕሮ የሞባይል መተግበሪያ እና በመላው

ሀገሪቱ ባሉ ከ1000 በላይ ቅርንጫፎቹ አማካይነት እንዲሁም ከ10,000 በላይ በሚሆኑ የባንኩ ወኪሎቹ ክፍያን መፈፀም የሚያስችል መተግበሪያ ለደንበኞች ማቅረባቸውን ጠቁመዋል።

አዋሽ ባንክ ቀደም ሲል በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ከበርካታ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በጋራ በመሥራት ላይ ይገኛል

**ጤና ሚኒስቴር ኢትዮጵያ**

ስልክ፡ +251-115-51-70-11

ፖ.ሳ.ቁ. 1234, Addis Ababa, Ethiopia

ኢ.ሜይል- info@moh.gov.et

**አዋሽ ባንክ (ብራንዲንግ እና ትሬድ ማርኬቲንግ ዳይሬክቶሬት)**

ስልክ፡ +251-115-57-01-67

ፖ.ሳ.ቁ. 12638

ኢ.ሜይል- SolomonJ@awashbank.com